
Bob Marley - Like it is- Interview 1980

ቦብ ማርሊ
Like it is' mic ላይ እንደእንግዳ ጋበዝንሃል

አመሰግናለሁ


LIGHT

Bob Marley - Like it is- Interview 1980

እንደእንግዳ ጋበዝንሃል Like it is' mic ላይ ቦብ ማርሊ
አመሰግናለሁ'

ጥ፡ -እንዴት ነው የተጀመረው ይሄ ሁሉ ነገር?
መ፡ -ልጅ እያለሁ ሙዚቃ ሁልጊዜ የህይወትህ አካል ነበር ?

ጥ፡ አዎ' የሙዚቃ ቤተሰብ ውስጥ ነው ያደኩት
መ፡ አያት' እናት' አጎት' እህት' ልጅ ሁሉም ታቃለህ'

ጥ፡ -ጃማይካ የት አካባቢ?
መ፡ Saint Ann' ታቃለህ' ገጠር አካባቢ ነው

ጥ፡ ምን ከተማ?
መ፡ ከተማው Road Nad' ብዙም አይታወቅም
ጋራው አካባቢ ያለ ትንሽ ቦታ ነው

ጥ፡ -ቤተሰብህ ምን ያህል ትልቅ ነው?

-

መ፡ ትልቅ ቤተሰብ ነው' የቤተሰቡ ስም Malcom' ይባላል
ትርጉሙ ብዙ' ማለት ነው

ጥ፡ -ጥሩ ስም ነው
መ፡ **አዎ**

ጥ፡ -መቼ ነው ሙዚቃ ውስጥ በደንብ መሳተፍ የጀመርከው?
መ፡ 1958 ምናምን አካባቢ ነው

ጥ፡ -ምን እየሰራህ?
መ፡ የሙዚቃ ፍላጎቱ ሁልጊዜ አለ ታቃለህ' በዛ ሰአት ግን ጊታር
እየተማርኩ እና መዝፈን የሚችሉ ሰዎችን መተዋወቅ ነበር
ከሰዎቹ አንዱ ዴዝመን ዴከር' ይባላል

አንድ ላይ መለማመድ ከዛ አንድ ቀን ሬከርድ የሚደረግበት
ቦታ ስንሄድ' ተከተልኩ እኔም

ጥ፡ -ያኔ የምትሰራው አይነት ሙዚቃ አይደለም አሁን
እየሰራህ ያለህው
-ምን አይነት ሙዚቃ ነበር መጀመሪያ ላይ?

መ፡ ያ ሙዚቃ ስካ' ይባላል

ጥ፡ -ስካ' ሙዚቃ ከሬጌ እንዴት ነው የሚለየው?

መ፡ ስካ በድምፅ ይለያል' በስታይል ይለያል' ስትጫወትም ይለያል' ታቃለህ' ስካ ፈጠን ያለ ሙዚቃ ነው ከሬጌ

ጥ፡ -ምንም አይነት ግንኙነት የለውም?

መ፡ ተከፋፍሎ ዝግ ስለሚል ነው እንጂ ሁልጊዜ ተመሳሳይ ሙዚቃ ነው'

ጥ፡ -ተመሳሳይ ስር'

መ፡ አዎ ' ሁሌ ተመሳሳይ ሙዚቃ ነው' ስካ 3ኛው ክር ላይ የምትጫወት ከሆነ ያንን ደግሞ 7 1/2 ላይ ነው' ገብቶኃል'

ጥ፡ -ጥሩ አገላለፅ ነው

-እንዴት ነው ስካ እና ሬጌ ከካሊፕሶ ሊወጡ የቻሉት ?

ብዙ ሰዎች ይጠይቃሉ ይሄን ነገር

መ፡ ካሊፕሶ ሁልጊዜ ለየት ይላል ታቃለህ ' እንደገና የጃማይካ ሙዚቀኞች ቡዙዎቹ ካሊፕሶ መጫወት ሲጀምሩ ምክንያቱም የአሜሪካ ሙዚቃ ተፅዕኖ እየመጣ

በዛ ሰአት ፋትስ ዳምኖ ' የሚባል ነበር እና ከዛ ጊዜ ጀምሮ ሙዚቃው ከሬጌ እየተንሸራተተ አፍ ብሎዝ' የሚባል አይነት ነገር ነበር' ስካ ከመምጣቱ በፊት ሲጫወቱ የነበረው ታቃለህ'

እንደ ጆ ሂግስ' አይነት ሰዎች ቻናናና ቻናናና ቻናናና ቻናናና' ታቀዋለህ ያን ዘፈን ?ያ ዘፈን ብዙ ጊዜ ተጫውቷል ስለዚህ ከዛ ሰአት ጅምሮ እያደገ ከዛ ሰዎች'

መ፡ ቼንቅ ቼንቅ ቼንቅ' -ስካ ታቃለህ'
ለ-ሮክ ስቴዲ ደግሞ 'ቼንግ ቼንግ ቼንግ'
የሬጌ ድምጽ ደግሞ 'እጩቅ እጩቅ እጩቅ' ታቃለህ

ስለዚህ አሁን 3 የተለያየ ስሜት አለህ' ግን አሁንም ሶስቱ
አንድ ላይ ሆነው አንድ ነገር መስራት ይችላሉ

ጥ፡ -አሁን ካሊፕሶ ሙዚቃ አብዛኛው ነገሩ ስለቤተሰብ' የሰዎች
ታሪክ' ፍቅር እና ቆንጆ ደሴት ከፀሐይ' ጋር አይነት ነገር ነው
-እንዴት ነው ዝግመተ ለውጡ ??
አሁን ከሙዚቃው መልዕክት ወደ ምናገኝበት የተሸጋገረው?

መ፡ ምክንያቱም ካሊፕሶ ሙዚቃ ምናምን በነበረበት ጊዜ
ሰዎች ስለአፍሪካ' ስለሙጡበት ስር ሀሊናቸው አልነቃም ነበር'
አሁን ሬጌ ከመጣ በኃላ ግን' ማለቴ ከሙዚቃ አንፃር ሳይሆን
ምክንያቱም ሙዚቃ ሁልጊዜ ከህሊና ጋር ነው

ሬጌ ከመጣ በኃላ ግን ሬጌ የሚያወራው ስለአፍሪካ ስለጥቁርነት
ታቃለህ' ወታደራዊ በሆነ መንገድ ማለት ነው ስለዚህ ለዛ ነው
ግጥሙ 'ቆንጆ ደሴት ከፀሐይ ጋር ምናምን' ከሚለው የሚለየው

ጥ፡ -ተፅዕኖቸህ ግን እነማን ናቸው?
መ፡ ትልቁ ተፅዕኖዬ ነው ብዬ የማስበው ማርከስ ጋርቬ 'ኃይለስላሴ'

ጥ፡ -ልጅ ሆነህ ስለጋርቬ የሰማህው ነው ወይስ ትልቅ
ሆነህ ስለሱ የተማርከው ነገር ነው ያነሳሳህ ?

መ፡ ከምንሰማው ከምናነበው ስለሱ ከምናውቀው

ጥ፡ -ስለጋርቬ ትምህርት ቤት ብዙ ተምረሃል?
መ፡ አይ አይ ትምህርት ቤት እንደዛ አይነት ትምህርት አናገኝም ታቃለህ' ስናድግ ነው እሱ ማን እንደሆነ ያወቅነው

ትምህርት ቤት የበለጠ የምናገኘው ትምህርት ክርስቶፈር ኮሎበስ' ማን እንደሆነ ማርኮ ፖሎ' ማን እንደሆነ እንጂ ማርከስ ጋርቬ' ማን እንደነበር ኃይለስላሴ' ማን እንደነበር ወይ ማንኛውም ጥቁር ሰው ማን እንደሆነ አናቅም

ጥ፡ -ራስታ ሆነህ ነው የተወለድከው?
-እንዴት ነው ቀስ እያለ የመጣው?

መ፡ እኔ እንዳረጋገጥኩት ከሆነ እንደዛ ነው የተወለድኩት ታቃለህ' ተወልጄ እያደኩ የሆነ ህሊናዊ ንቃት ነበረኝ በኔ ውስጥ ግን የብቸኝነት አለም ነበር' እንደኔ የሚያስቡ አይነት ሰዎች ምናልባት አይኖሩ ይሆን የሚለው ነገር ታቃለህ'

የማስበው ነገር የተለየ ነው አይነት ሳይሆን' ይሄ ህሊና እግዛብሔር እና ሰዎች የመጡበት የሚለው ነገር ክርስትያኖች ናቸው በብዛት ታቃለህ '

እና ሁልጊዜ ግን እኛ ትክክል አይደለም ከሚለው ነበር መቆም ምንሞክርው' የምንፈልግ የነበረው' ግን እናገኝ የነበረው አንዱ ቤተ ክርስትያን ከሌላኛው ቤተ ክርስትያን ሲጋጭ ነበር ታቃለህ '

እና እኔ ሳገናዝበው እንደሱ አይነት ነገር እንደማልፈልግ ገባኝ የምር አንዱ ከሌላኛው እየተጣላ አሁንም ሁለቱም ስለእግዛብሔር ያወራሉ

መ፡ ስለዚህ እየሄድኩ እየሄድኩ መጣሁ ታቃለህ' ሚያጠነክርህ ነገር ከኪንግስተን ነው የመጣው ብዙ ሰዎች ስትገናኝ እነዛ ሰዎች ራስታ' ናቸው

ታዋራቸው እና የምታገኘው ነገር ተመሳሳይ ነው ወይ ውስጣቸው ያለው ተመሳሳይ ነው

ጥ፡ -እድሜህ ስንት ነበር ይሄ ነገር ሲጀመር ?

መ፡ ይሄ 17' 18' ምናምን ነገር ቢሆን ነው' የምታገኘው ነገር ራስታ ሰው እንደሚያወራው ተመሳሳይ ነገር ሆነ' ስለዚህ እንደዛ ነው ራሴን ልለየው የምችለው እንደራስታ ባለመቀየር ታቃለህ'

ጥ፡ -ምን አጋጠመህ ወደ ቤተሰቦችህ ተመልሰህ ያገኘህውን ስትነግራቸው?

መ፡ እረ የምመለስበት ቤት አልነበረኝም' ሁሉም ሄደው ነበር ታቃለህ' ሁሉም ሄደዋል' አንዳንዶዎቹ አሜሪካ አንዳንዶዎቹ ኪንግስተን ሄደዋል

ቤት የነበረን አያታችን ከመሞቱ በፊት ነበር ታቃለህ' አያታችን ከሞተ በኃላ ሁሉም ነገር ፈረሰ

ጥ፡-ከዛ በኃላ ኪንግስተን መጣህ እና ነገሮቹ ጀመሩ? አዎ
-ኪንግስተን ውስጥ የት አካባቢ ነበር ትኖር የነበረው?

መ: East ነበር የሚባለው East Kingston ከምስራቅ በኩል ከዛ ከላይኛው፣ ከላይኛው መንገድ Oxford street እስከሚባለው ድረስ እንሄድ እና ከዛ ወደታች Spanish Town መንገድ ከዛ Trench town መንገድ ላይ እንጨርሳለን

ጥ: -አሁን ለረጅም ጊዜ ነገሮች መስመር የያዙ ይመስላል?

መ: አዎ' ነገሮች መስመር የያዙ ሊመስል ይችላል እንደስራህ እና እንደምጠብቀው ነገር ታቃለህ'

ለኔ ነገሮች መስመር የያዙ ይመስላሉ ግን አልቻልኩትም ምክንያቱም ከገጠር ነገሮችን ተምረህ ስትመጣ' ልክ ቤተሰብህ ላይ ጥገኛ አለመሆን ምናምን ታቃለህ'

ትወጣ እና የራስህን በቆሎ ትተክላለህ እና በቆሎው ሲያድግ ታያለህ' በቆሎ ሲያድግ የራስህን በቆሎ ትለቅማለህ ገብቶኃል' ሌሎቹም ፍራፍሬዎች ሁሉ ዛፍ ላይ አሉ ማግኘት ትችላለህ ታቃለህ '


ጥ: -ከተማ ውስጥ ግን ትንሽ ለየት ይላል ኧ? አዎ -ብዙ ለየት ያሉ ነገሮች እንሰራለህ ለመብላት 'አዎ

መ: ከተማ ውስጥ በጣም ለየት ያለ የመላጣ ጭዌ ነው ታቃለህ' ሰዎች ስራ መሄድ አለባቸው' ባስ ይዘህ ትመለሳለህ ወደቤት' ገጠር ግን አህያን ይዘህ ተርጋግተህ ወደማሳ እየነዳህ ትሄዳለህ

ከተማ ውስጥ ግን ሰዎች ስራ መሄድ አለባቸው' ባስ ይዘህ ትመለሳለህ ወደቤት ታቃለህ' ለየት ያለ ነገር ነው እዚህ ያለው

ጥ፡ -ስለጃማይካ ትንሽ ነገር አቃለሁ እና ኪንግስተን ውስጥ Trench Town ጠጠር ያለ ሰፈር ነው እንዴት ተረፍክ?

መ፡ እንግዲህ Trench Town እንደታዳጊ ስትኖር ለመትረፍ ቀላል ነው ማየት የሚጠበቅብህ ነገር ፖሊስ ብቻ ነው ገብቶኃል' ምክንያቱም ፖሊስ ከያዘህ እስር ቤት ትገባለህ ምክንያት ከትረንች ታዎን ስለመጣህ ታቃለህ' ከየት ነው የመጣህው? ትባል እና ''ትረንች ታዎን'' ስትል' በቃ ሄደሃል' ገብቶኃል' ያሳፍሩኃል'



ጥ፡ -ብዙ ሰዎች ራስታ ምን እንደሆነ በጣም ግራ ይገባችዋል
ብዙ ጊዜ እንደውም አሉታዊ የሆነ ምስል ነው ያላቸው ስለራስታ
ራስታ ምን እንደሆነ እስቲ ንገረን ?

መ፡ አየሀ' ክርስቶስ ተመልሶ እንደሚመጣ ቃል ገብቷል'
በዚህ 2000 አመት ውስጥ ታቃለህ'
እና እሱም ተመልሶ ሲመጣ

'ንጉሰ ነገስት የጌቶች ጌታ ሞአ አንበሳ ዘ እምነገደ ይሁዳ ይሆናል
በንጉስ ሰለሞን እና በንጉስ ዳዊት መስመር' ይላል

አሁን የኔ ህይወት ትልቅ ትርጉም አለው ለኔ

ስለዚህ አምላክ እዚህ እንዳለ መፈለግ አለብኝ

መ፡ ስፈልግ ሁሉም ጋር ተመልክቻለሁ ወደ ኢትዮጲያ ፈለኩ
ጀርመንም ፈለኩ አድሎ እንዳይኖር '' አምላክን
ፈለኩ ' ኢትዮጲያን ስመለከት' በዚህ ስም የቆመ አንድ
ሰውዬ አየሁ

'ንጉስ ኃይለስላሴን ስሙም ንጉሰ ነገስት የጌቶች ጌታ ሞአ አንበሳ
ዘ እምነገደ ይሁዳ
በንጉስ ሰለሞን እና በንጉስ ዳዊት መስመር ይሆናል'
መፀሐፍ ቅዱሱ ላይ ተጽፏል

ሙ፡ እሱ ላይ የኔ ነገር ምንድነው King James መፀሐፍ ቅዱስን edit አርጓል የሚሉት ነገር ነው የኔ አረዳድ ምንድነው King James መፀሐፍ ቅዱስን edit ቢያደርግ ኖሮ ለጥቁሮች ጥቅም ሲሊ edit ያረግዋል ብዬ አላስብም'

ስለዚህ አሁን ራዕዩ ሲገለፅ ኃይለስላሴ ንጉሰ ነገስት የጌቶች ጌታ በንጉስ ሰለሞን እና በንጉስ ዳዊት መስመር ሲሆን ታቃለህ' ያኔ አወቅን የክርስቶስ መመለስ ይሄ እንደሆነ

ምክንያቱም በዚህ አለም ላይ ስትኖር ነጭ ሰው edit ሲያደርግ' በኛ በኩል ያደላ አድርጎ አይፅፈውም'' edit ካደረገው edit የሚያደርገው England ትልቅ ነገር እንደሆነች አድርጎ ነው ታቃለህ'

በስተመጨረሻ ግን እውነቱ ሲወጣ ኢትዮጲያ ኃይለስላሴ ሆነ ታቃለህ' የኃይለስላሴ ስም ደግሞ ራስ ተፈሪ ነው ለዛ ነው በስሙ የምንጠራው'

ሙ፡ ሌላም ብዙ ነገር አለው እና እሱም ሲመለስ 'ይሄ አምላክ ነው ሴሜን ስትጠራው እናት እና አባቶችህ ይጠብቁኃል ይልኃል ' አሁን እንደምናውቀው ካቶሊኮቹ ጋር ከሄድክ ይቀበሉኃል' አምላክን ቤተ ክርስትያን ውስጥ የምትጠራው ከሆነ ይቀበሉኃል'

የትኛውም አይነት ሃይማኖት ቢሆን ሊቀበልህ ይችላል ከሁሉም የሚገፋህ ብቸኛ ሃይማኖት ግን ራስታ ነው እንደዛ ሲሆን ነው የበለጠ እውነቱ የምር የሚሆነው

ምክንያቱም ሴሜን ስትጠራው እናት እና አባቶችህ ይጠብቁኃል ይልኃል፣ ለዛ ነው ዛሬ ራስታ መጥፎ ስም ያገኘው

ምክንያቱም ራስታ መጥፎ ነገር ስለሚያደርግ ሳይሆን ትንቢቱ ነው የመራው፣ እናት እና አባቶችህ ከጠበቁህ አስበው፣ የሚያውቁህ ሰዎች ደግሞ ገብቶኃል፣

ጥ፡ -ብዙ ሃይማኖቶች ላይ እሁድ እሁድ ትሄዳለህ፣ ምናልባት አንድ ሁለት ጊዜ በሳምንት ውስጥ የመፀሐፍ ቅዱስ ትምህርት ይኖራል በቃ ያ ነው፣

-ተመሳሳይ ነገር ነው በራስታ ወይስ የበለጠ ተሻሽሎ ተቀይሯል?

መ፡ አይደለም፣ እኛ እያልን ያለነው ቤተ ክርስትያኑ ነው የታመመው መፀሐፍ ቅዱሱ እዛው ነው ያለው

አሁን ስናይ ግን ብዙ ሰዎች መፀሐፍ ቅዱስ ያነባሉ ግን መፀሐፍ ቅዱሱን ግን አይረዱትም

ምክንያቱም መፀሐፍ ቅዱሱን የቀረቡበት መንገድ የተሳሳተ ነው፣ አባባሌ መፀሐፍ አንስተህ ከመሃል ዝም ብለህ አታነብም ከመጀመሪያው እስከመሃል እያነበብክ ነው የሆነ ነገር ምትፈልገው

መፀሐፍ ቅዱሱ ሙሉ መፀሐፍ ነው፣ ከነሙሉ ባህል' ስታነብ ከኦሪት ከዘፍጥረት እስከ ራእይ' ሙሉ እውነቱ ቀጥታ ነው መንገዱ፣ ለራስህ ትክክል አድርገህ የምትረዳው እዛ ላይ ነው ያለው ታቃለህ፣

እና ቤተ ክርስትያን ሄዶ ሌሎች ክርስትያኖችን ማስደስት ነገር ሳይሆን እኛ የምናቀው ቤተ ክርስትያኑ እንደታመመ ነው ታቃለህ'

ምክንያቱም እውነቱን ዝም ብለህ መወርወር አትችልም ታቃለህ' እኛ ሰዎች ስር አለን' ስንፈልገው ራስታ ላይ አገኘነው

ምክንያት ሌላ መንገድ አላየንም' ሌላ መንገድ አላየንም ራስታ ላይ ነው ስራችንን ያገኘነው ታቃለህ'

ጥ፡ ታዋቂነትን እንዴት ቻልከው ?

መ፡ ታዋቂነትን የቻልኩት ታዋቂ ባለመሆን ነው

ጥ፡ እረ ታዋቂ ሰው ነህ

መ፡ አይ' ማለቴ ለኔ አደለሁም' እኔ ታዋቂ አይደለሁም ለራሴ' አየህ ተማርኩ ተማርኩ' ከአሜሪካ ስመጣ' ሙዚቃ ከጀመርኩ ጀምሮ ታቃለህ' እኔን ከማይፈልጉኝ ሰዎች

ስማ' ይሄ ጨዋታ ጨዋታ ነው' ጭንቅላትህን የማትሸጥ ከሆነ ህሊናህን ታጣለህ'

ስለዚህ ህሊናህን የምታጣበት ብቸኛ መንገድ ያ ከሆነ' አንዳንድ ሰዎች እንደሚሉት ጭንቅላትህ ሊያብጥ ይችላል' ጭንቅላትህ ካበጠ ደግሞ በቃ'

ስለዚህ እኔ ጭንቅላቴን የማያብጥበት
ቦታ ነው የማስቀምጠው ታቃለህ'
እውነት'

ጥ፡ -ሴቶቹን እንዴት ቻልካቸው?ሰዎች ይታያቸዋል ሴቶች
ይመጡብሃል' በሩን እየደበደቡ ቦብ ማርሌን ለማግኘት' ልብስ
ይይዛሉ' ምናምን እንደዛ ነገር ነው?

መ፡ አይደለም '
ሴቶች ቀለል' ቀስ' ያሉ ናቸው ታቃለህ'

ጥ፡ -ሚዛንህን ለመጠበቅ አስቸጋሪ ነው ግን ?
ጠቃሚ ሰው እንደሆንክ አይነት ሰዎች
በተለያዩ ነገሮች ካንተ ጋር በሚሆኑበት ጊዜ?

መ፡ አይደለም' ምክንያቱም እራሴን እንደዛ አይቼው አላውቅም'
አቃለሁ ለህዝቡ ጠቃሚ እንደሆንኩ ታቃለህ' ያ ነው የኔ ብቸኛ
ያለኝ ሀሊና' ለህዝቡ ጠቃሚ መሆን እችላለሁ የሚለው
ታቃለህ' ሌላ ነገር ምንም አላውቅም

ጥ፡ -ቦብ ማርሌ የሚለውን ስም ትልቅ
ያደረገው ነገር ምንድነው ብለህ ታስባለህ?

መ፡ እንደማስበው ከሆነ ምናልባት ቦብ ማርሌ ስለቆመለት
ነገር ይሆናል

ጥ፡ ምንድነው እሱ?
መ፡ ለእውነት'
በህይወት ለመቆየት እና ለመትረፍ ቆራጥነቱ ታቃለህ'

⊓LIGHT

Vol-1

ጥ፡ ጥያቄ
መ፡ መልስ (ቦብ)


rLIGHt

ጥ፡ -በህይወት ስለመቆየት 'ሰርቫይቫል የሚል ቅጂም አለህ ?
መ፡ አዎ ባለፈው አመት ነው እሱ

ጥ፡ -አንተ ላይ የተከሰተብህ ነገር አለ እሱን ለመጻፍ
ምክንያት የሆነህ ?

መ፡ 1976 በጥይት ተመትቼ ነበር አይደል
ሳስበው እሱ በህይወት መቆየቴ እንደሆነ ገባኝ

ጥ፡ -ምንደነው የሆነው በጥይት በተመታህበት ጊዜ?
-ቤትህ ነበርክ? ጡዋት ነበር? ምሽት ምንድነው የሆነው?

መ፡ ምሽት 3:00 አካባቢ ነበር' የሆነው ነገር ከመሆኑ
ከ3 ቀን በፊት Bullbay የሚባል ቦታ እኖር ነበር ታቃለህ'

8:00 ሰዓት አካባቢ ነበር የሄድኩት ትንሽ ለመተኛት
ከዛ በጣም ብዙ የተኩስ ሩምታ ውስጥ ነበርኩ ታቃለህ'
ያ ህልም ነበር የተኩስ ሩምታ ውስጥ ነበርኩ

ተነስቼ ሳይ ግን በጥይት የተመታሁበት ቦታ የለም
እናቴ ግን ተመታለች ታቃለህ' እይታው እንዳሳየው
እናቴ ጭንቅላቷ ላይ እንደተመታች ነው

እና እይታው አትሩጥ' አለ ልክ በዛ ሁሉ የተኩስ ሩምታ
ውስጥ ከእይታው የሆነ ነገር አትሩጥ' አለ
'ቁም'

እና የጥይት ተኩሱ Hope Road እንደተሰማ'
የመጀመሪያው ጭንቅላቴ ውስጥ የመጣው ነገር ያ እይታ ነው

ከእይታው የማስታውሰው ነገር ሁሉ አትሩጥ' ያለውን ነበር
ቁም' ከዛ ቀጥብዬ ቆምኩ

ከዛ ታቃለህ' የተኩስ ፍልሚያም አልነበረም
ጥይቱ እስኪያልቅ ተኮሱ እና መሮጥ ጀመሩ' ተርጋጋ ነገር

ጥ፡ -የቱ ጋር ነው የተመታህው? የቱ ጋር ነው የተመታህው?
መ፡ እዚህ ክርኔ ላይ

ጥ፡ -በስቶት አለፈ?
መ፡ አይ ውስጥ ትልቅ ነገር ነው' ያሉት

ጥ፡ -ተኪሹን ግን በጭራሽ አላየኸውም?
መ፡ በዛ ጊዜ አላየሁትም

ጥ፡ -ግን ማን እንዳረገው አውቀኸዋል?
መ፡ አዎ

ጥ፡ -ተይዟል?
መ፡ አይ' ፖሊስ መያዝ ምናምን እንኪን
አለ አ' የሰው ነገር

ጥ፡ - የሬከርድ ካምፓኒ አለህ አሁን?
መ፡ አዎ

ጥ፡ -ለምን ?
መ፡ የሬከርድ ካምፓኒ ከረጅም ጊዜ በፊትም ነበረን
የሌለን ዘፈን መቅጃ ስቱድዮ ነበር

ስቱድዮ ለመስራት በምንሄድበት ጊዜ ብዙ ፍትጊያ አለው
ታቃለህ' እኛ ራስታ ነን' አንዳንድ ሰዎች ራስታ ስቱድዮአቸው
ውስጥ እንዲሰራ አይፈልጉም እና ይሄን ሁሉ ስታይ አንድ
የራስህን መስራት ያስፈልግኃል ገብቶኃል አባባሌ'

የሆነ ሰው ምናልባት ኃይለስላሴ አምላክ ነው ትላለህ' ሄደህ
የራስህን ስቱድዮ ገንባ ሊልህ ይችላል ገብቶኃል' እሺ ኃይለስላሴ
አምላክ ነው ብዬ የራሴን ስቱድዮ ሰራሁ ታቃለህ'

እና ስለዚህ የሆነ ሊጨቁኑህ ምናምን ነው ሚፈልጉት ገብቶኃል'
እንጂ ሁሉም ነገር አሪፍ ቢሆን ስቱዲዮ መገንባትም
አይጠበቅብንም ግን ሸዋጅ የሆነ ቦታ ነው'

ሁሉም ሰብዓዊ የሆነ ስሜት የለውም ታቃለህ' አንዳንዶቹ
ሰዎች የተስማማህበትን ነገር እንኳን አይገባቸውም

ጥ፡ -የቦብ ማርሌ ወደፊት ምንድነው አጀንዳው? ታቀዋለህ'
-ውይስ ማስተር ፕላን አለህ ?

መ፡ እኔ እና እኔ ወደፈት የአፍሪካ አንድነት ነው'
የአፍሪካ አንድነት ከመጣ በኃላ ሰዎች ማየት መረዳት
ይጀምራሉ ገብቶኃል'
እዚህ ነገር ውስጥ ይሆነ ነገር አለው አይነት'

ጥ፡ -እራስህን አፍሪካዊ እንደሆንክ ነው የምታስበው
ጃማይካዊ ከመሆን ፈንታ?አዎ

መ፡ ምክንያቱም ዋናው ነገር ራስታ ነን' ራስታ መሆንህን ስትቀበል
ኢትዮጲያዊ ነው የምትሆነው ' እሱም አፍሪካ

የሚቀጥለው ነገር ደግሞ የጃማይካ ታሪክ እንደሚያሳየው
Arawak Indians የሚኖረው እዛ ነው
Arawak Indians ነን

አሁን ታሪካችን እንደሚያሳየው በባሪያ ንግድ ምክንያት
ጥቁር ህዝብ ወደ ምዕራቡ የወጡበት አይነት ነገር ነው ታቃለህ'
እና አፍሪካ ስራችን ነው ታቃለህ'
እንደተባለውም መመለስ አለብን

ጥ፡ -ምንድነው በብዛት ሚታይህ
የአፍሪካ ችግር' ከአንድነት ባለፈ?

መ፡ የአፍሪካ ችግር የማየው ከህዝቡ ውጭ ሰዎች የሚደክሙት ነገር
ነው' ነገሮችን አንድ ለማድረግ እንኳን የሚያቅታቸው ገብቶኃል'
ይሄኛው ኃያል ካልሆነ ወይ ያኛው'

ግን አፍሪካ ብቸኛ ቦታ ነች' ለብቻዋ ልትጠቀምባት የምችልባት
ታቃለህ' ማንም በደንብ አላወቀውም' አፍርካ በጣም ሃብት
ያላት ናት'

አፍሪካ የሆነ ሰው የሆነ ነገር ሰርቆ ወደ ውጭ የዘባት የሚሄድ'
አፍሪካ እየጠበቀች አይነት ነገር '
ግን አፍሪካ ዝግጁ ናት'

ጥ፡ -ጋርቪ 'አፍሪካ ለ አፍሪካዊያን' ነው የሚለው
አንተም እንደዛ ነው የሚሰማህ ?

መ፡ አዎ' 'አፍሪካ ለ አፍሪካዊያን
ውጭ ያለ ሞኖርያ' ገብቶኃል'
እውነት'

ጥ፡ -መኖሪያ ቤትህ ጃማይካ እንደሆነ ነው የሚቆየው ወይስ የሆነ ጊዜ ወደ አፍሪካ ነው ?

መ፡ አይ' የሆነ ጊዜ ወደ አፍሪካ ነው ምናልባት እየሩሳሌም ገብቶኃል' የመጻሐፍ ቅዱስ ምድር'

ጥ፡ -ስለጃማይካ ወደፊት ምንድነው የምታስበው?

መ፡ ስለጃማይካ ወደፊት የምታስበው ጃማይካ ቆንጆ ደሴት ናት በጣም ቆንጆ የምትሆነውን ያህል ልክ እንግሊዝ ጃማይካ እንደነበረች ጃማይካም የሆነ ነገሯ አፍርካ እንደሆነች ነገር መስራት አለባት ገብቶኃል' የተሻለ አሪፍ ይሆናል

ግን የሚሆነው ነገር ሁልጊዜ ጦርነት አለ ምክንያት ብቸኛው መፍትሄ ብለው ራሳቸውን ከናይጄርያ ያደርጋሉ ወይ ከሆነ ሰው ገብቶኃል' ግን ጃማይካም የሆነ ነገሯ አፍርካ እንደሆነች ነገር መስራት አለባት አፍሪካ ጃማይካ ላይ እንደነበረች አይነት

ግን ሰዎች ሁልጊዜ የሚመጡበት ነገር ላይ የሚቀናቸው ነገር ሃሳብ ወይ ፍልስፍና ነው የሆነ ሰው ማርክሲስት' የሆነ ሰው ይሄ የሆነ ሰው ያ' ብዙ ሰዎች የማይሉት ግን አፍሪካዊያንን ነው አፍሪካ ደግሞ የራሷ ባህል የራሷ ህዝብ አላት ታቃለህ' የሚያስፈልገን ነገር ሁሉ' አለን

ጥ፡ -አሜሪካ ውስጥ ላሉት ጥቁር ህዝቦች ሁኔታ ምንድነው ስሜትህ?

መ፡ የሚሰማኝ ነገር ጥቁር ህዝቦች ራሳቸውን ማሳደግ አለባቸው ገብቶኃል' አድሎ አይነት ያለው እድገት ሳይሆን የራሳችን ታሪክ' የራሳችን ባህል' ያለን ህዝቦች ነን እራሳችንን ማስተማር እንችላለን' ማለቴ እኛ የመጀመሪያ ፍጡራኑ እኮ ነን

እዚህ ምድር ላይ የምታየው ነገር ሁሉ ጥቁር ህዝብ ነው የሰራው ነጩ ህዝብ የሆነ ነገር አልሰራም እያልኩ ሳይሆን ሁሉም ጥበብ ግን የመጣው ከጥቁር ህዝብ ነው'

ጥ፡ -ታቃለህ' ብዙ ታዳጊ ተመልካቾች ወዳንተ ያያሉ እና እያንዳንዱን ቃል እያንዳንዱን ክፍለ ቃል ይይዛሉ -ለታዳጊ ሰዎች መልዕክት አለህ?

መ፡ እንግዲህ ታቃለህ' በድጋሚ ሁሉም ነገር እውነቱን የምር ማየት ነው' የራስታን' የሆነ በስህተት ማሻማት አይነት ሳይሆን

እራስህን በስራ አትጥመድ እውነቱን ላለማረጋገጥ ምክንያቱም እውነቱ እዛ ነው እና አፍሪካ ፍጥረቷን ትጠብቃለች'

እንደምናውቀው ደግሞ በምዕራቡ ያሉ ሰዎች አዋቂ ሆነዋል' ተዘጋጅተዋል ታቃለህ'

በምዕራቡ የተማርከውን ወደቤት አምጥተህ ለህዝቡ እንዲጠቅም ታደርገዋለህ' ምክንያቱም ማለቴ እስከመቼ ነው ጥቁር ህዝብ መሰቃየት ያለበት ታቃለህ'

እና የራሳችን ባህል አለን' ሁሉም ነገር አለን' ምንም ነገር አያጥረንም' ሁሉም ነገር አለን' በተጨማሪ ቦታ አለን ግን ማንም አይኖርበትም እና ወደእሱ መሄድ አለብን

ማለቴ ስትሄድ ይሄንን ትልቅ ህንፃ መገንባት ትችላለህ' ከፈለክ ከተማ ካጣህ ከተማ መገንባት ገብቶታል' መኪና ከፈለክ መኪና ማግኘት ትችላለህ'

ማለቴ ትልቅነቱ አይታየኝም፣ አንድ ጊዜ አሜሪካ የተለያዩ ብዙ ያለፉ ነገሮች ነበሯት ልትል' ትችላለህ

አፍሪካ ሰላማዊ ቦታ ናት

ጥቁሩን ህዝብ የሚጃጅሉት በቅራቅቦ ምናምን ብቻ ነው፣

ጥ፡- አፍሪካ ውስጥ የት የት ሄደሃል ከኢትዮጲያ በስተጎን?
መ፡ ዚንባብዌ
ጋቦን

ጥ፡ -ዚንባብዌን እንዴት አገኘህው?
መ፡ ዚንባብዌ አሪፍ ዚንባብዌ የምርም በጣም አሪፍ ማለቴ ገነት የሆነ ቦታ ላይ ታቃለህ' ሄደህ ስታይ የምታየው ቆንጆ ነገር ነው

ጥ፡ -የህዝቡን ምላሽ እንዴት አገኘህው?
መ፡ ህዝቡ ትልቅ፣ ህዝቡ ጥሩ ናቸው ታቃለህ'

ሄደህ ስታይ ሰዎች የሚኖሩት እንደቦታው አቀማመጥ ነው እና ከቦታው አካባቢውን ወጣ እያልክ ማየት ትችላለህ ገብቶኃል' ውጭ ያለው አካባቢ በጣም ያምራል

አንበሳ ምናምን ማየት ከፈለክ በቃ፣ በእግርህ ራመድ ብለህ ማየት ትችላለህ' የሆነ ሰው ያልሰራው ነገር ማየት ከፈለክ ደግሞ፣ ግን የሆነ ሰው የሰራው ሲመስል እንደዛም አይነት ነገር ናት ዚንባብዌ ምክንያቱም የሆነ ቦታ ትሄድ እና ድንጋይ የተደራረበ ታያለህ' ሰው እንዳልሰራው ስታቅ' ግን ቅርፁ የተሰራበት መንገድ ታቃለህ' ከሆነ ነገር በላይ ነው

-የምር መረጃ የሞላበት ደስ የሚል ጭውውት ነበር ካንተ ጋር ’
-ወንድሜ ማርሊ’
አሪፍ’

-አመሰግናለሁ ለጊዜህ’
አይሬ’

-መልካሙን ሁሉ እመኝልኃለው’

ΓLIGHϽ

LIGHT

Rights

You are permitted to use the resources for any number of personal projects, If you wish to promote this resource on your site, you have the rights to redistribute, however any credit will be much appreciated.

Prohibitions

You do not have the rights to modify or intended for sale this material

Yoseph Birhanu

yosephb764@gmail.com

Addis Ababa 2012 E.C

ᑭ_ㅂ

ᒥLIGHᒣ